## 29. የሚያጠራ የቃሉ እሳት ተሰጥቶሃል

"በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፤ ድንጋዩንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር።" (ኤር. 23፡29)

"እኔም የእግዚአብሔርን ስም አላነሳም ከእንግዲህ ወዲህ በስሙ አልናገርም ብል፤ በአጥንቶቼ ውስጥ እንደ ገባ እንደሚነድ እሳት ያለ በልቤ ሆነብኝ ደከምሁ፤ መሸከምም አልቻልሁም።" (ኤር. 20፡9)

"እርስ በእርሳቸው፦ በመንገድ ሲናገር መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።" (ሉቃ. 24፡32)

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እሳት ለምን ይጠቅማል?

- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___

2. የቃሉ እሳት በሰው ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ሥራ ዘርዝር።

- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___

## 30. የሚያነጻ የቃሉ ውኃ ተሰጥቶሃል

"ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ።" (ኤፌ. 5፡26)

"እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፤ በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ።" (ዮሐ. 15፡3)

"ለባሪያህ መልካም አድርግ ሕያው እንድሆን፤ ቃልህን እንድጠብቅ።" (መዝ. 118፡17)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ውኃና የእግዚአብሔር ቃል የሚመሳሰሉበትን ባህርያት ዘርዝር?

- 
- 
- 
- 
- 

2. በቃሉ የመንጻት አስፈላጊነት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ቃሉ የሚያነጻው ምናችንን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 31. ሕይወትህን የሚያሳይ የቃሉ መስተዋት ተሰጥቶሃል

"ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮን ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደ ምን እንደሆነ ይረሳል።" (ያዕ. 1፡23)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የመስታወት ጥቅም ምንድን ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

2. ቃሉ ከመስታወት ይልቅ ይበልጣል ብለህ ታስባለህ? እንዴት?

♦
♦
♦
♦
♦

## 32. የሚያጠግብ የቃሉ እንጀራ ተሰጥቶሃል

"ሰውም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ፤ አስራበህም ያላወቅኸውን አባቶችም ያላወቁትን መና አበላህ።" (ዘዳ. 8፡3)

"ቃልህ ተገኝቶአልና እኔም በልቼዋለሁ፤ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ።" (ኤር. 15፡16)

"ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፤ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕጻናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።" (1ጴጥ. 2፡2)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ቃሉ ከምግብ ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ዘርዝር።

♦
♦
♦

- 
- 

2. የተመጣጠነ ምግብ መብላት ለሰውነት አስፈላጊ ከሆነ ለመንፈሳዊ ሕይወትስ ምሳሌነቱ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

## 33. የሚመራ የቃሉ ብርሃን ተሰጥቶሃል

"ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው።" (መዝ. 118፥103) "የቃልህ ፍቺ ያበራል፤ ሕጻናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።" (መዝ. 118፥130)

"ትዕዛዝ መብራት፤ ሕግም ብርሃን ነውና፤ የተግሣጽም ዘለፋ የሕይወት መንገድ ነውና፤" (ምሳ. 6፥23)

"ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፤ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።" (2ጴጥ. 1፥19)

**የውይይት መነሻ ጥያቄዎች**

1. የብርሃንን ጥቅም ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 
- 

2. የጨለማን ጉዳት ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 
- 

3. የቃሉን ጠቀሜታ ከብርሃን አንጻር አወዳድር?

- 
- 
- 
- 
- 

4. ቃሉ የሚያበራው ምናችንን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

## ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ተስፋዎች

ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡት ተስፋዎች በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑት የተሰጡ ስለሆነ በእምነት ተቀብሎ ለሚለማመዳቸው ክርስቲያን ሁሉም የእርሱ ናቸው። ከቁጥር 34 እስከ 44 የተጠቀሱት የመንፈስ ቅዱስ ተስፋዎች ለክርስቲያኖች የተሰጡ ናቸው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራና የጸጋ ስጦታዎች ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. መንፈስ ቅዱስ ያለ ፈቃዳችን በሕይወታችን ውስጥ የሚፈጽማቸው ነገሮች ይኖራሉን?

- 
- 
- 
- 
- 

2. መንፈስ ቅዱስ የሚያስገድደን ስለየትኞቹ የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ይመስልሃል?

♦
♦
♦
♦
♦

3. ለግለሰብና ለቤተ ክርስቲያን ተስፋዎቹ የተሰጡት ምን ለማድረግ ይመስልሃል?

♦
♦
♦
♦
♦

4. የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ዋንኛው ዓላማ ክርስቶስን ለማስከበር፤ ሰዎችን ወደ መንግሥቱ ለማምጣትና የመጡትንም ለማነጽ ወይም ለማሳደግ ስለሆነ ተቀባዩ ሊረዳቸው የሚገቡት ነገሮች ምንድን ናቸው ብለህ ታስባለህ?

♦
♦
♦
♦
♦
♦
♦
♦
♦
♦

5. ስጦታዎች ሁሉ ከልሳን ስጦታ በስተቀር በአጠቃላይ የተሰጡት ለምንድን ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

6. የመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ስጦታ ምንድነው?

♦
♦
♦
♦
♦

7. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

8. መንፈስ ቅዱስ ራሱ ማን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

9. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 

10. ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበልካቸው ስጦታዎች ምንድነው ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

11. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለነማን ይሰጣል? ለምንስ ጥቅም?

- 
- 
- 
- 
- 

12. በክርስትና ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንና ምንን ያጠቃልላል?

- 
- 
- 
- 
- 

13. በጸጋ ስጦታና በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል ያሉት ልዩነቶች ምንድን ናቸው?

- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____

14. በመንፈስ መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው?

- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____
- ♦ ____

## 34. በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ተሰጥተውሃል

"ነገር ግን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጣል።" (ሮሜ 8፡11)

## 35. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ተሰጥተውሃል

"መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።" (ኤፌ. 5፡18)

"እግዚአብሔር ይላል በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤" (ሐዋ. 2፡17)

## 36. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሰጥቶሃል

"እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፣ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።" (ሉቃ. 24፡49)

"...በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።" (ዘካ. 4፡6)

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።" (ሐዋ. 1፡8)

"እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን..." (ኤፌ. 3፡20)

"ንስሐ ግቡ ኃጢያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" (ሐዋ. 2፡38)

## 37. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ተሰጥቶሃል

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል፤ ለታሰሩትም መፈታትን፤ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፤ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ፣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል።" (ሉቃ. 4፡18)

"እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ።" (1ዮሐ. 2፡20)

"እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፤ በእርሱ ኑሩ።" (1ዮሐ. 2፡27)

## 38. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተሰጥቶሃል

"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፤ ደስታ፤ ሰላም፤ ትዕግሥት፤ ቸርነት፤ በጎነት፤ እምነት፤ የውሃት፤ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።" (ገላ. 5:22–23)

## 39. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተሰጥቶሃል

"እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩዋቸው በእያንዳንዳቸው ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።" (ሐዋ. 2፡3–4)

"ስለዚህ፦ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል።" (ኤፌ. 4፡8)

"ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።" (1ቆሮ. 12፡11)

"ንስሐ ግቡ ኃጢያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" (ሐዋ. 2፡38)

የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች በዝርዝር ስንመለከታቸው የሚከተሉትን እናስተውላለን። (1ቆሮ. 12፡8–10፤ 1ቆሮ. 12፡28፤ ሮሜ 12፡6–8፤ ኤፌ. 4፡11፤ 1ጴጥ. 4፡11)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የሚከተሉትን ነጥቦች አብራራ?

- በጥበብ መናገር

◆ ________________________
◆ ________________________
◆ ________________________
◆ ________________________

- እውቀትን መናገር

◆ ________________________
◆ ________________________
◆ ________________________

- እምነት
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- የመፈወስ ስጦታ
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- መናፍስትን መለየት
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- ተአምራትን ማድረግ
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- ልሳኖችን መተርጎም
- ♦
- ♦
- ♦
- ♦

- ትንቢት መናገር
- ♦
- ♦
- ♦

- ረዳትነት
- 
- 
- 
- 

- መስጠት
- 
- 
- 
- 

- ሌሎችን ማጽናናት
- 
- 
- 

- ሐዋርያነት
- 
- 
- 
- 

- ነቢይነት
- 
- 
- 

- አስተማሪነት
- 
- 
- 
- 

- መጋቢነት
- 
- 
- 
- 

- ወንጌላዊነት
- 
- 

- 
- 
- 

- **እስተዳዳሪነት**
- 
- 
- 
- 

- **መምከር**
- 
- 
- 
- 

- **ማስተማር**
- 
- 
- 
- 

- **መማር**
- 
- 
- 
- 

- **አገልግሎት**
- 
- 
- 
- 
- 
- 

- **መግዛት**
- 
- 
- 
- 

2. ከላይ ከተዘረዘሩት አሉኝ የምትላቸው ስጦታዎች የትኞቹ ናቸው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

3. ስጦታህን በምን ታውቃለህ?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

4. በስጦታህ ምን ያህል ተጠቅመሃል?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

5. ስጦታህን ለማሳደግ ምን ጥረት እያደረግህ ነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

## 40. ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘው ቅድስና ተሰጥቶሃል

## 41. የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተሰጥቶሃል

"በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።" (ገላ. 5፥18)

"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።" (ሮሜ 8፥14)

## 42. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት አለህ

"የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።" (ሮሜ 8፥16)

## 43. መንፈስ ቅዱስ ያስተምርሃል

"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።" (ዮሐ. 14፡26)

"ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤" (ዮሐ. 15፡26)

## 44. መንፈስ ቅዱስ ይጸልይልሃል (ይማልድልሃል)

"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንደምንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።" (ሮሜ 8፡26–27)

ከመንፈስ ቅዱስ ተስፋዎች ጋር የተሰጡ ስድስት ያህል ማስጠንቀቂያዎች የሚከተሉት ናቸው፦

**44.1** መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝን፦ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" (ኤፌ. 4፡30)

**44.2** መንፈስ ቅዱስን እንዳንቃወም፦ "እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፤ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ።" (ሐዋ. 7፡51)

**44.3** ድምፁን ስንሰማ ልባችንን እልከኛ እንዳናደርግ፦ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፦ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት

የመረመሩበት አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደ ሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።" (ዕብ. 3፡7–9)

44.4 መንፈስ ቅዱስን እንዳናጠፋ፦ "የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና። መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤" (1ተሰሎ. 5፡19)

44.5 በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንዳንዋሽ፦ "የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ስለ ምን ተስማማችሁ? እነሆ፤ …ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? …እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም" (ሐዋ. 5፡9 ና 3–4)

44.6 መርምረን ከጌታ የሆነውን መንፈስ እንድንቀበልና ከእርሱ ያልሆነውን መንፈስ እንድናርቅ፦ "መንፈስን አታጥፉ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።" (1ተሰሎ. 5፡20)

"ከገባው የተስፋ ቃል መሠረት ለሕዝቡ ሰላምን የሰጠው እግዚአብሔር ይመስገን፤ በአገልጋዩ በሙሴ አማካይነት የሰጠውን መልካም የተስፋ ቃል ሁሉ ጠብቆአል።" (1ነገ. 8፡56 የ1980 ዓ.ም ትርጉም)

"እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ሁሉ "አዎን" የሚሆነው በክርስቶስ ነው፤" (1ቆሮ. 1፡20 የ1980 ዓ.ም ትርጉም)

# ክ ፍ ል – አ ራ ት

## ለተለያዩ ሰዎችና ሁኔታዎች የተሰጡ ተስፋዎች

ለግለሰብና ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡት ተስፋዎች በተጨማሪ ለተለያዩ ሰዎች የተሰጡ የተስፋ ቃል ኪዳኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘርዝረዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ አባት ለሌላቸው፤ ለመጻተኞች፤ ለባልቴቶች፤ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ፣ በእግዚአብሔር ለሚታመኑ፤ ለጻድቃን፤ በእግዚአብሔር መንገድ ለሚሄዱ፤ እግዚአብሔርን ለሚፈልጉ የተሰጡትን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን። በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ሰዎች ከዚህ ቀጥለው ያሉትን ተስፋዎች የራሳቸው በማድረግ ሊኖሩበት የሚችሉት ራሳቸውን ለክርስቶስ ጌታነት ቢያስገዙ ነው።

### 1. አባት ለሌላቸው አባት ይሆናቸዋል።

"ለድሀ አደጉና ለመበለቲቱ ይፈርዳል፤ መብልና ልብስም ይሰጠው ዘንድ ስደተኛውን ይወድዳል።" (ዘዳ. 10፥18)

### 2. ለመበለቶች ይፈርድላቸዋል።

"ለድሀ አደጉና ለመበለቲቱ ይፈርዳል፤ መብልና ልብስም ይሰጠው ዘንድ ስደተኛውን ይወድዳል።" (ዘዳ. 10፥18)

### 3. ለድሆች መጠጊያ ይሆናል።

"እግዚአብሔር ለድሆች መጠጊያ ሆናቸው፤ እርሱም በመከራቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው።" (መዝ. 9፥9)

"ድሀ ለዘላለም አይረሳምና፤ የችግረኞችም ተስፋቸው ለዘላለም አይጠፋም።" (መዝ. 9፥18)

## 4. ለመጻተኞችና ለስደተኞች ይጠነቀቅላቸዋል።

"እናንተ በግብፅ ምድር ስደተኞች ነበራችሁና ስደተኛውን አትበድለው ግፍም አታድርግበት።" (ዘፀ. 22፥21)

"በስደተኛው ግፍ አታድርጉ፤ እናንተ በግብፅ ምድር ስደተኞች ስለ ነበራችሁ የስደተኛ ነፍስ እንዴት እንደ ሆነች አውቃችኋልና።" (ዘፀ. 23፥9)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ቤተክርስቲያንና እያንዳንዱ ክርስቲያን ለድሆች ሊኖራቸው የሚገባው ኃላፊነት ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? (ገላ. 2:9-10)

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

2. እግዚአብሔር ለድሆች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

3. ክርስቶስ የተቀባው ለድሆች ወንጌልን ለመስበክ ከሆነ ከድሆች ጋር ለመሥራት ምን ያስፈልጋል ትላለህ?

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

4. የእውነተኛ ኃይማኖት መለኪያ ምንድነው? (የያዕቆብ መልእክትን አጥና)

- ____
- ____
- ____
- ____
- ____

# እግዚአብሔርን ለሚፈሩት የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. ለሚፈሩት ጥበብን ይሰጣቸዋል

"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ለሚያደርጉትም ሁሉ ደህና ማስተዋል አላቸው፤ ምስጋናውም ለዘለዓለም ይኖራል።" (መዝ. 110፡10)

## 2. ለሚፈሩት ረዥም ዕድሜን ይሰጣቸዋል

"እግዚአብሔርን መፍራት ዘመንን ታስረዝማለች።" (ምሳ. 10፡27)

## 3. ለሚፈሩት የሕይወትን ምንጭ ይሰጣቸዋል

"ሰው ከሞት ወጥመድ ያመልጥ ዘንድ እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት ምንጭ ነው።" (ምሳ. 14፡27)

"እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት ይመራል፤ የሚፈራውም ጠግቦ ይኖራል፤ ክፉ ነገርም አያገኘውም።" (ምሳ. 19፡23)

## 4. የሚፈሩትን ያስተምራቸዋል

"እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ትምህርት ነው፤ ትህትናም ክብረትን ትቀድማለች።" (ምሳ. 15፡33)

## 5. የሚፈሩት በሥራቸው ይባረካሉ

"የድካምህን ፍሬ ትመገባለህ፤ ምስጉን ነህ መልካምም ይሆንልሃል። እነሆ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል።"(መዝ. 127፡2 ና 4)

## 6. የሚፈሩት በሕይወታቸው ይባረካሉ

"እግዚአብሔርን የሚፈራ ትዕዛዙንም እጅግ የሚወደድ ሰው ምስጉን ነው። ክብርና ባለጠግነት በቤቱ ነው ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል።" (መዝ. 111፥1 ና 3)

## 7. የሚፈሩት ቤተሰባቸው ይባረካል

"ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት፤ ልጆችህም በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው። እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል። እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የኢየሩሳሌምን መልካምነትዋን ታያለህ። የልጆችህንም ልጆች ታያለህ።" (መዝ. 127፥3–6)

## 8. የሚፈሩትን ይጠብቃቸዋል

"የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል።" (መዝ. 33፥7)

## 9. ለሚፈሩት ምሕረቱን ያበዛላቸዋል

"ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ።" (መዝ. 109፥11)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው የተባለው ለምንድ ይመስልሃል?

- ◆ ____________________________________________
- ◆ ____________________________________________
- ◆ ____________________________________________
- ◆ ____________________________________________
- ◆ ____________________________________________

2. እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው?

- ◆

♦
♦
♦
♦

3. ሰው እግዚአብሔርን ከመፍራት ቸል የሚለው ለምን ይመስልሃል?

♦
♦
♦
♦
♦

4. እግዚአብሔርን ያለ መፍራት ወደ ምን ይመራል?

♦
♦
♦
♦
♦

5. እግዚአብሔርን የመፍራታችን ምልክቱ ምንድነው?

♦
♦
♦
♦
♦

6. እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር የሚከተሉት በረከቶች ምንድን ናቸው?

♦
♦
♦
♦
♦

# ለጻድቃን የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. የእግዚአብሔር ዓይኖች በጻድቃን ላይ ናቸው

"የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸው።" (መዝ. 33፥15)

## 2. ጻድቃንን አይተዋቸውም

"...እርሱ ራሱ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና..." (ዕብ. 13፥5)

"እናንተ የያዕቆብ ቤት ሆይ የእስራኤልም ቤት ቅሬታ ሁሉ ከሆድ ያነሣኋችሁ ከማህፀንም የተሸከምኋችሁ ስሙኝ፣ እስከ ሽምግልና ድረስ እኔ ነኝ፤ እስከ ሽበትም ድረስ እሸከማችኋለሁ፤ እኔ ሠርቻለሁና እኔ እነሣለሁ እኔ እሸከማለሁ እኔም አድናለሁ።" (ኢሳ. 46፥3–4)

## 3. ለጻድቃን መሸሸጊያቸው ይሆናል

"የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል።" (ምሳ. 18፥10)

## 4. ለጻድቃን መንገዳቸውን ያበራል

"የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፣ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል።" (ምሳ. 4፥18)

## 5. ለጻድቃን ኃይላቸው ይበዛል

"ጻድቅ ግን መንገዱን ያጠነክራል እጁም ንጹህ የሆነ ሰው ኃይልን እየጨመረ ይሄዳል።" (ኢዮ. 17፥9)

## 6. ጻድቃን አይራቡም

"ጎለመስሁ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል ዘሩም እህልን ሲለምን አላየሁም።" (መዝ. 36፥25)

## 7. ጻድቃን መልካም ነገር አይጎድልባቸውም

"እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም።" (መዝ. 83፥11)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የጻድቃን ተስፋቸው ታላቅ ከሆነ ጻድቃን የሚባሉት እነማን ናቸው?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

2. የጽድቃችን መሠረቱ ምንድነው?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

3. ከቁጥር 1-7 ያሉት እውነታዎች በሕይወትህ ውስጥ እንደሚንጸባረቁ ለመመስከር ትደፍራለህን?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

# እግዚአብሔርን ለሚሰሙት የተሰጠ ተስፋ

## 1. ያለ ስጋት ይኖራሉ

"የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፤ ከመከራም ስጋት ያርፋል።" (ምሳ. 1፥33)

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔርን መስማት ማለት ምን ማለት ነው?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

♦
♦

2. ጌታ ጆሮ ያለው ይስማ ሲል ምን ማለቱ ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

3. እግዚአብሔርን ለመስማት ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

♦
♦
♦
♦
♦

# እግዚአብሔርን ለሚጠባበቁ የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. የሚጠባበቁት አያፍሩም

"...እኔንም በመተማመን የሚጠባበቁ አያፍሩም።" (ኢሳ. 49፥23)

## 2. የሚጠባበቁት ኃይላቸውን ያድሳሉ

"እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ ይሮጣሉ፤ አይታክቱም ይሄዳሉ አይደክሙም።" (ኢሳ. 40፥31)

## 3. የሚጠባበቁትን ይሰማቸዋል

"ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ።" (መዝ. 39፥1)

## 4. ለሚጠባበቁት ይራራላቸዋልና ብፁዓን ናቸው

"እግዚአብሔርም የፍርድ አምላክ ነውና ስለዚህ እግዚአብሔር ይራራላችሁ ዘንድ ይታገሣል፤ ይምራችሁም ዘንድ ከፍ ከፍ ይላል እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ ብፁዓን ናቸው።" (ኢሳ. 30፥18)

## 5. የሚጠባበቁት ደስ ይላቸዋል

"እነሆ አምላካችን ይህ ነው፤ ተስፋ አድርገነዋል፤ ያድነንማል፤ እግዚአብሔር ይህ ነው፤ ጠብቀነዋል፤ በማዳኑም ደስ ይለናል ሐሴትም እናደርጋለን ይባላል።" (ኢሳ. 25፥9)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን በመጠበቅ ኃይላችንን የምናድሰው እንዴት ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔርን መጠበቅ የሚለው ሃሳብ ምን ትርጉም ይሰጥሃል?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. እግዚአብሔርን መጠበቅ አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. ከቁጥር 1-5 ያሉትን ተስፋዎች በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የምትወስዳቸውን እርምጃዎች በዝርዝር አመልክት?

- 
- 
- 
- 

# እግዚአብሔርን ለሚፈልጉት የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. በነፍሳቸውና በልባቸው ከፈለጉት ያገኙታል

"ነገር ግን ከዚያ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትሻላችሁ በልብህም ሁሉ በነፍስህም ሁሉ የፈለግኸው እንደሆነ ታገኘዋለህ።" (ዘዳ. 4፡29)

"ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያ አንኳኩ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልገውም ያገኛል፤ መዝጊያም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።" (ማቴ. 7፡7–12)

## 2. የሚፈልጉት ይጸናሉ

"እግዚአብሔርን ፈልጉት ትጸናላችሁም፤ ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ።" (1ዜና 16፡11)

## 3. የሚፈልጉት ሥራቸው ይቃናላቸዋል

"እግዚአብሔርንም መፍራት ባስተማረ በዘካርያስ ዘመን እግዚአብሔርን ይፈልግ ዘንድ ልብ አደረገ እግዚአብሔርንም በፈለገ ጊዜ እግዚአብሔር ነገሩን ሁሉ አከናወነለት። ...ስለ እግዚአብሔርም ቤት አገልግሎት በጀመረው ሥራ ሁሉ፣ በሕጉና በትዕዛዙም፤ አምላኩን ለመፈለግ በፍጹም ልቡ አደረገው ተከናወነለትም።" (2ዜና 26፡5፤ 31፡21)

## 4. ለሚፈልጉት ታላቅን ነገር ያደርጋል

"እኔ ግን እግዚአብሔርን እለምን ነበር ነገሬንም ወደ እግዚአብሔር አቀርብ ነበር። የማይመረመረውን ታላቅ ነገር የማይቆጠረውን ተአምራት ያደርጋል።" (ኢዮ. 5፡8–9)

"ወደ እኔ ጩህ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።" (ኤር. 33፡3)

## 5. የሚፈልጉትን አይተዋቸውም

"ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ፤ አቤቱ የሚሹህን አትተዋቸውምና።" (መዝ. 9፡10)

## 6. የሚፈልጉትን ከመከራቸው ያድናቸዋል

"እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፤ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።" (መዝ. 33፡4)

## 7. የሚፈልጉት መልካም ነገርን አያጡም

"ባለጠጎች ደኸዩ ተራቡም፤ እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ግን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጎድሉም።" (መዝ. 33፡10)

## 8. የሚፈልጉትን ጌታ ይሰማቸዋል

"ቆይቼ እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት፤ እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ።" (መዝ. 39፡1)

## 9. የሚፈልጉት ማስተዋል አላቸው

"ክፉዎች ሰዎች ፍርድን አያስተውሉም እግዚአብሔርን የሚሹ ግን ሁሉን ያስተውላሉ።" (ምሳ. 28፡5)

## 10. የሚፈልጉት በሕይወት ይኖራሉ

"...እኔን ፈልጉ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ፤" (አሞጽ 5፡4)

## 11. ለሚፈልጉት ይገናኛቸዋል

"አንተም ልጄ ሰሎሞን ሆይ፤ እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና፤ የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና የአባትህን አምላክ እወቅ፤ በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው ብትፈልገው ታገኘዋለህ ብትተወው ግን ለዘላለም ይጥልሃል።" (1ዜና 28፡9)

"...እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ስትሆኑ እርሱ ከእናንተ ጋር ነው፤ ብትፈልጉትም ይገኝላችኋል ብትተውት ግን ይተዋችኋል።" (2ዜና 15፡2)

"ምድርም ተከፈተች ዳታንንም ዋጠችው፤ የአቤሮንንም ወገን ደፈነች፤" (መዝ. 105፡17)

### <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት ምን ማለት ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. እግዚአብሔር የምንፈልገው እንዴት ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. እግዚአብሔርን ከመፈለግ ቸል እንድንል የሚያደርገን ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

4. ከቁጥር 1-11 የተዘረዘሩት እግዚአብሔርን የመፈለግ ውጤቶች ለመንፈሳዊ እድገታችን እንዴት ይጠቅሙናል?

- 
- 
- 
- 
- 

## ለሚያምኑት የተሰጡ ተስፋዎች

### 1. የሚያምኑት ያልተወሰነ የጌታ ኃይል አላቸው

"ኢየሱስም ቢቻልህ ትላለህን ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።" (ማር. 9፡23)

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" (ዮሐ. 14፡12)

### 2. የሚያምኑት የጸሎት መልሳቸውን ያገኛሉ

"ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁ እመኑ፤ ይሆንላችሁማል።" (ማር. 11፡24)

### 3. ለሚያምኑት የሕይወት መሰናክሎች አይጋርጧቸውም

"የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፤ ይህን ሾላ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት ይታዘዝላችሁ ነበር።" (ሉቃ. 17፡6)

## 4. የሚያምኑት እርካታ አላቸው

"በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።" (ዮሐ. 12፡46)

## 5. የሚያምኑት የአገልግሎት ኃይል አላቸው

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" (ዮሐ. 14፡12)

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን በማመንና በእግዚአብሔር በመታመን መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. እምነት ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

3. የእምነት መሠረቱ ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

4. የእምነት ውጤቱ ምንድነው?

- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___

5. ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ማለት ምን ማለት ነው?

- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___

6. በእምነት ለማደግ ምን ማድረግ ይገባናል?

- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___
- ◆ ___

# ራሳቸውን ዝቅ ለሚያደርጉ የተሰጠ ተስፋ

## 1. ጌታ ከፍ ያደርጋቸዋል

"እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ" (1ጴጥ. 5፥6)

"ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፤ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።" (ማቴ. 23፥12)

"በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።" (ያዕ. 4፥10)

# ለቸሮች የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. ቸሮች ከመከራ ይድናሉ

"ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔር ከክፉ ቀን ያድነዋል።" (መዝ. 41፡1)

## 2. ቸሮች በረከትን ያገኛሉ

"እግዚአብሔርን ከሃብትህ አክብር፤ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት ጎተራህም እህልን ይሞላል፤ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።" (ምሳ. 3፡9–10)

## 3. ቸሮች ብልጽግናን ይቀበላሉ

"የምትባረክ ነፍስ ትጠግባለች፤ የረካም እርሱ ደግሞ ይረካል።" (ምሳ. 11፡25)

"ትዕዛዜን ብትሰማ ኖሮ ሰላምህ እንደ ወንዝ ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር፤ ዘርህም እንደ አሸዋ የሆድህም ትውልድ እንደ ምድር ትቢያ በሆነ ነበር።" (ኢሳ. 48፡18–19)

## 4. ቸሮች ፍጹም ተስፋ ይኖራቸዋል

"ከመካከልህ ቀንበርን ብታርቅ፤ ጣትህንም መጥቀስ ብትተው፤ ባታንጎራጉርም፣ ነፍስህንም ለተራበ ብታፈስ፤ የተጨነቀውንም ነፍስ ብታጠግብ፤ ብርሃን በጨለማ ይወጣል ጨለማህም እንደ ቀትር ይሆናል።" (ኢሳ. 58፡10)

## 5. ቸሮች የተትረፈረፈ በረከት ያገኛሉ

"ስጡ ይሰጣችሁማል በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፤ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።" (ሉቃ. 6፡38)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ቸርነት ምንድነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

2. ቸርነት የማን ባሕርይ ነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

3. ቸርነት ማሳየት ያለብን መቼ ነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

4. የቸርነት ጥቅሙ ለማን ነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

5. በበረከት የመዝራት ምስጢሩ ምንድነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

6. ከአሥር እጅ የመጀመሪያውን የማይሰጥ ሰው ንፉግ ሳይሆን ለምን ሌባ ተባለ?

♦
♦
♦
♦
♦

7. ክርስቲያን ንፉግ ሆነ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

## በንስሐ ለሚመለሱ የተሰጡ ተስፋዎች

### 1. የሚመለሱትን ያድናቸዋል

"እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።" (መዝ. 33፡18)

### 2. የሚመለሱትን ይፈውሳቸዋል

"ከዳተኞች ልጆች ሆይ ተመለሱ፤ ከዳተኝነታችሁንም እፈውሳለሁ እነሆ አንተ አምላካችን እግዚአብሔር ነህና ወደ አንተ እንመጣለን።" (ኤር. 3፡22)

### 3. ለሚመለሱት ይራራላቸዋል

"ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፣ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፤ ቁጣው የዘገየ፤ ምሕረቱም የበዛ፤ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።" (ኢዩ. 2፡13)

## 4. የሚመለሱትን ይቅር ይላቸዋል

"በደልን ይቅር የሚል፣ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምሕረትን ይወድዳልና ቁጣውም ለዘላለም አይጠብቅም።" (ሚክ. 7፡18)

## 5. የሚመለሱ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ

"ንስሐ ግቡ ኃጢያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" (ሐዋ. 2፡38)

## 6. ለሚመለሱት የመታደስ ጊዜ ይሰጣቸዋል

"እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ፣ ኃጢያታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም።" (ሐዋ. 3፡19)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ንስሐ ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. በመጸጸትና በንስሐ መካከል ልዩነት አለ ወይ? ካለ ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. ንስሐ መግባት የሚያመለክተው ምንን ነው?

- ______
- ______
- ______
- ______

4. ንስሐ የሚገቡ ይፈወሳሉ ሲል ምን ማለቱ ነው?

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

5. ክርስቲያን ንስሐ የሚገባው መቼ ነው?

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

◆ ____________________________________________________

# እርሱን ለሚያገለግሉ የተሰጡ ተስፋዎች

## 1. የሚያገለግሉት እንደ ሰማይ ከዋክብት ያበራሉ

“ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ጸዳል፤ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።” (ዳን. 12፥3)

## 2. የሚያገለግሉት ይሸለማሉ

“የክርስቶስ ስለ ሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውኃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለሁ።” (ማር. 9፥41)

“ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤” (1ቆሮ. 3፥14)

“እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።” (ራዕ. 22፥12)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. አገልግሎት ምንድነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

2. አገልግሎት የሚጀምረው የት ነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

3. የእውነተኛ አገልግሎት ፍሬ ምንድነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

4. እውነተኛ አገልጋይ በምን ይታወቃል?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

5. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ የሚባለው ማን ነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

# ክ ፍ ል – አ ም ስ ት

## ክርስቲያኖች የሚጠባበቋቸው የወደፊት ተስፋዎች

### 1. ጌታ ተመልሶ ይመጣልናል

"ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፤ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።" (ዮሐ. 14፡1–3)

"የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፤ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።" (ሐዋ. 1፡11)

### 2. የተባረከ ተስፋ ይጠብቀናል

"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ ኃጢያተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፤ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፤ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፤ መልካሙን ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፤ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።" (ቲቶ 2፡11–14)

### 3. አንድ ቀን በቅጽበተ–ዓይን እንለወጣለን

"እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፤ ከቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።" (ፊል. 3፡21)

"እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።" (1ቆሮ. 15፥51-52)

## 4. በአየር ጌታን ለመቀበል እንነጠቃለን

"ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስም የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፤ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።" (1ተሰ. 4፥16-17)

## 5. የሕይወት ትንሣኤ ይጠብቀናል

"እግዚአብሔር ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሳናል።" (1ቆሮ. 6፥14)

"ጌታ ኢየሱስን ያስነሣው እኛን ደግሞ ከኢየሱስ ጋር እንዲያስነሣን ከእናንተም ጋር እንዲያቀርበን እናውቃለን።" (2ቆሮ. 4፥14)

"በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።" (ዮሐ. 5፥28)

## 6. የትንሣኤን ሥጋ እንለብሳለን

"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፤ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ ደግሞ አለ።" (1ቆሮ 15፥42-44)

## 7. ጌታን ፊት ለፊት እናየዋለን

"ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።" (1ቆሮ. 13፥12)

"እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፤ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።" (ራዕይ 1፥7)

"ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግንባሮቻቸው ይሆናል።" (ራዕይ 22፥4)

## 8. ጌታን ወደ መምሰል እንለወጣለን

"ወዳጆች ሆይ፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።" (1ዮሐ. 3፥2)

## 9. በእጅ ያልተሠራ ቤት ይጠብቀናል

"ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፤ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና። በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃተታለን፤ ከሰማይ የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም።" (2ቆሮ. 5፥1–2)

"በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፤ እኔ ባለሁበት እናንተም ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።" (ዮሐ. 14፥2–3)

## 10. የመንግሥቱ ወራሽ እንሆናለን

"ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።" (ማቴ. 25፡34)

## 11. ተወዳዳሪ የማይገኝለት ክብር በሰማይ ተዘጋጅቶልናል

"ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ እንዲህ እንናገራለን።" (1ቆሮ. 2፡9)

## 12. አዲስ ስም የተቀረጸበት ነጭ ድንጋይ ይሰጠናል

"መንፈስ ለአቢያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፤ ነጭ ድንጋይም እሰጠዋለሁ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።" (ራዕ. 2፡17)

## 13. ለበጉ ሠርግ ተጠርተናል

"ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጎናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና። እርሱም፦ ወደ በጉ ሠርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ።" (ራዕ. 19፡8–9)

## 14. የለቅሶና የዋይታ ዘመናችን ያበቃል

"ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፤ ሌሊትና ቀንም በመቅደስ ያመልኩታል፣ በዙፋኑም የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፣ ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሙም፤ ጸሐይም ትኩሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ

እረኛቸው ይሆናልና፤ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባቸውን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።" (ራዕ. 7፡15–17)

"...እንባዎችን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ኃዘንም ቢሆን ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤..." (ራዕ. 21፡4)

## 15. እግዚአብሔር ለዘላለም አምላካችንና አባታችን ይሆናል

"እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መከከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።" (ራዕ. 21፡3)

"ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።" (ራዕ. 21፡7)

## 16. የአገልግሎት ሽልማት ተዘጋጅቶልናል

"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።" (ራዕ. 22፡12)

"ሰውም፤ በእውነት ለጻድቅ ፍሬ አለው፤ በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ ይላል።" (መዝ. 57፡11)

እንደ ታማኝነታችን የተለያዩ ሽልማቶች ይሰጡናል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉት የሽልማት ዓይነቶች እንዳሉ ያረጋግጥልናል፦

16.1 እንደ ሰማይ ከዋክብት ማብራት፦ "ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፤ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።" (ዳን. 12፡3)

16.2 የጽድቅ አክሊልን መቀበል፦ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውንም ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ

ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።" (2ጢሞ. 4፥7–8)

16.3 የሕይወት አክሊልን መውረስ፦ "የትዕግሥቱን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።" (ራዕ. 3፥10) እንዲሁም ያዕ. 1፥12 ተመልከት።

16.4 የማይጠፋ አክሊልን መቀዳጀት፦ "የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፤ እኛ ግን የማይጠፋውን።" (1ቆሮ. 9፥25)

16.5 የክብርን አክሊልን መቀበል፦ "የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ።" (1ጴጥ. 5፥4)

16.6 የደስታ አክሊል፦ "የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፤ ደስታዬና አክሊሌ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ፤" (ፊል. 4፥1) እንዲሁም 1 ተሰ. 2፥19 ተመልከት።

## 17. አሕዛብን እንገዛለን

"ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልኩት በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፤ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፤ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ።" (ራዕ. 2፥26–28)

"ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?" (1ቆሮ. 6፥2–3)

## 18. በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ለዘላለም እንኖራለን

“ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፦ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።” (ራዕ. 21፡2–3)

“በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ ወሰደኝ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤” (ራዕ. 21፡10–11)

“የተናገረኝም ከተማይቱና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።” “ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሠራ ነበረ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጌጦ ነበር፤ ፊተኛው መሠረት ኢያስጲድ፣ ሁለተኛው ሰንፔር፤ ሦስተኛው ኬልቄዶን፤ አራተኛው መረግድ፤ አምስተኛው ሰርዶንክስ፤ ስድስተኛው ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፤ ስምንተኛው ቢረሌ፤ ዘጠነኛው ወራውሬ፤ አሥረኛው ክርስጵራስስ፤ አሥራ አንደኛው ያክንት፤ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ። አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ እያንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቊ የተሠራ ነበረ። የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።” (ራዕ. 21፡15፤ 18–21)

## 19. ከጌታ ጋር እንነግሣለን

“ዙፋኖችንም አየሁ፤ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፤ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግንባራቸው በእጆቻቸው ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤

ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ። የቀሩት ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም።" (ራዕ. 20፡4–5)

## 20. ጌታ ሁሉንም አዲስ ያደርግልናል

"በዙፋኑም የተቀመጠው፦ እነሆ፤ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ። አለኝም፦ ተፈጽሞአል።" (ራዕ. 21፡5)

## 21. የጌታን አዲስ ስም እንቀበላለን

"ስሙም በግንባሮቻቸው ይሆናል።" (ራዕ. 22፡4)

"ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፤ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፤ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፤ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።" (ራዕ. 3፡12)

## 22. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን እንወርሳለን

"አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ባሕርም ወደ ፊት የለም።" (ራዕ. 21፡1)

## 23. ከጌታ ጋር ለዘላለም በክብር ትኖራለህ።

"እነሆ፤ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፤" (ራዕ. 21፡3)

"ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።" (ራዕ. 22፡5)

"ይህን የሚመሰክር፦ አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፤ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ቶሎ ና።" (ራዕ. 22፡20)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ዳግም ምጽዓት ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ጌታ በክብር ታጅቦ የሚመጣው መቼ ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. የዳግም ምጽዓቱ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

4. ጌታ ለምንድነው ዳግም ተመልሶ የሚመጣው?

- 
- 
- 
- 
- 

5. የክርስቲያኖች ታላቁ ደስታ የጌታ ዳግም ምጽዓት ከሆነ ጌታን እንዴት መጠበቅ አለብን?

- 
- 
- 
- 
- 

6. ጌታ ዳግም ሲመለስ በሕይወታችን ውስጥ ከሚፈጸሙት ነገሮች መካከል ሃያ ሦስቱ ከዚህ በላይ ተዘርዝረዋል። የተቀሩትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አክልባቸው።

- 
- 
- 

◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________

7. ስለ ጌታ መመለስ ከሚያጓጉህ ነገሮች መካከል ሁለቱን ጥቀስ?

◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________

8. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ቢመጣ ልትቀበለው ተዘጋጅተሃል?

◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________
◆ ______________________________________________

# መመሳከሪያ

ስለ እግዚአብሔር ተስፋዎች በእንግሊዝኛ ከተጻፉት መጽሐፍት ውስጥ የሚከተለው መጽሐፍ ነው ጠቃሚ ሃሳብ ሊሰጥ ይችላል ብዬ የማስበው ።

Lockyer, Herbert (1962) "All The Promises of the Bible", Lamplighter Books: Grand Rapids, U.S.A

# GOSPEL OF GLORY

## የ ክ ብ ሩ ወ ን ጌ ል

የክብሩ ወንጌል አገልግሎት ጥልቀት ያላቸውን መንፈሳዊ መጻሕፍትንና አውደ ጥናቶች በማዘጋጀት በመንፈሳዊ አገልግሎት ዙሪያ የተሰማሩትን ቤተ ክርስቲያናትንና አማኞችን ለማገልገል የተቋቋመ መንፈሳዊ ድርጅት ነው። ይህ መጽሐፍ የዚህ አገልግሎት አንዱ ፍሬ ነው። ለአስተያየትም ሆነ ስለ አገልግሎቱ በይበልጥ ለማወቅ እንዲሁም ከአገልግሎቱ ጋር ለመተባበር በሚከተለው አድራሻ ሊጽፉልን ይችላሉ።

Gospel of Glory
P. O. BOX 62537
Colorado Springs, Co.80962, USA
E-mail gg@goglory.org